dc water is life®

LEAD FREE DC

ጥያቄ ወይም እገዛ ይፈልጋሉ? ያነጋግሩን፦
(202) 787-4044 ወይም
lead@dcwater.com

David L. Gadis, Chief Executive Officer

DISTRICT OF COLUMBIA WATER AND SEWER AUTHORITY | 1385 CANAL STREET, SE | WASHINGTON, DC 20003

# የመግቢያ ፈቃድ
# በቦታዬ ላይ የውሃ ቱቦውን <u>በነጻ</u> ለመተካት

እባክዎ ሁሉንም አስፈላጊ ቦታዎች ይሙሉ፣ አለበለዚያ የፈቃድ ቅጹ ተቀባይነት አይኖረውም።

ሌድ ወይም ሌድ ከያዙ የውሃ ቱቦዎች የሚመነጨው ሌድ ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ እና/ወይም ለነዋሪዎች ጎጂ ሊሆን ይችላል። ይህ ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ እና/ወይም ለነዋሪዎቹ የሌድ ተጋላጭነትን መቀነሻ እርምጃ ስለሆነ የDC Water ባለ ሌድ የውሃ ቱቦዎችን መተካት ይፈልጋል ነገርግን የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልገናል። ይህ የመግቢያ ፈቃድ ማለት የሌድ የውሃ ቱቦዎችን በአዲስ የኮፐር (የመዳብ) የውሃ ቱቦዎች **በነጻ፣ ለእርስዎ ያለምንም ወጪ** ለመተካት የDC Water እና የሥራ ተቋራጫችን ወደ ግል ቦታዎ እንዲገቡ ለመፍቀድ ተስማምተዋል ማለት ነው። ይህ ፈቃድ በተጨማሪም በግል ቦታዎ ላይ ሥራውን እንዳይሰሩ ሊያደርጓቸው ስለሚችሉ ወይም ቧንቧዎችዎን በሚተኩ ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ ስለሚያውቋቸው ማናቸውም **የተደበቁ አደጋዎች** ለDC Water ለመንገር ይስማማሉ ማለት ነው። **እባክዎን ያስተውሉ፦** እንዲሁም ፈቃድ ካለው የቧንቧ ሠራተኛ ጋር በሕንጻዎ ውስጥ ያሉ ሌሎች የሌድ ቧንቧዎችን ምንጮችን ለይቶ እንዲያውቅ እና እነሱንም ለማስወገድ እንዲያስብበት እንመክርዎታለን።

**የDC Water የሥራ ተቋራጭ የሚያደርገው የሚከተለውን ነው (ተያያዡን ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ)፦**

1. ለስምንት (8) ሰዓታት አካባቢ የሕንጻዎን የውሃ አገልግሎት ማቋረጥ፤
2. የዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር፣ መቆጣሪያው እና የቦታው ወሰን አጠገብ መቆፈር እና የሌድ የውሃ ቱቦዎን በመንገድ ላይ ካለው ዋና የውሃ መስመር በሕንጻዎ ግድግዳ ወይም ወለል ውስጥ ካለው የቧንቧ ግንኙነት ማላቀቅ፤
3. ቧንቧው ወደ ሕንጻዎ በሚገባበት እና ውስጥ ካለው የውሃ መስመር ጋር በሚገናኝበት ግድግዳ በኩል መንገድ ላይ ካለው ከዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር እስከ ህንፃዎ ድረስ አዲስ **የኮፐር የውሃ ቱቦ** ማስገባት፤ እና
4. ውሃውን ከፍቶ፥ የተቦረቦሩ ቀዳዳዎችን ደፍኖ፣ ቦታውን ወደነበረበት መልሶ እና ከተቻለ ውሃውን ከውጭ ቱቦ ግንኙነት ማፍሰስ።

**መጠበቅ የሚገባዎት የሚከተሉትን ነው፦**

1. **የሥራ ተቋራጩ <u>ለእርስዎ ያለ ምንም ወጪ</u> በግል ቦታዎ ላይ የሌድ ውሃ ቱቦውን በኮፐር የውሃ ቱቦ ይተካል።** ሠራተኞቹ የመተካት ሥራውን ለመሥራት የግል ቦታዎ ላይ እና ሕንጻዎ ውስጥ ይገባሉ። በመጀመሪያ የውሃ ቱቦው ከምን እንደተሠራ ለማረጋገጥ የቦታው ወሰን ላይ ጉድጓድ ይቆፍራሉ። አንድ ጊዜ ካረጋገጡ በኋላ፣ ከላይ ያሉትን ደረጃዎች ይከተላሉ፣ ምናልባትም በሌላ ቀን። ከመተከሉ በፊት፣ በጊዜው፣ እና በኋላ ፎቶዎችን እና ቪዲዮዎችን ያነሳሉ።

2. **የሥራ ተቋራጩ የግል ቦታዎን እንዳገኘው ወይም ከዛ በተሻለ ሁኔታ ለመተው ይሞክራል።** የሥራ ተቋራጩ ድራይዎሎችን፣ ንጣፎችን፣ ግድግዳዎችን፣ አጥሮችን፣ ቁጥቋጦዎችን፣ የእግረኛ መንገዶችን፣ የመኪና መግቢያ መንገዶችን፣ ድንጋዮችን፣ ሳርን፣ አበባዎችን፣ እፅዋትን ወይም ሌሎች በቦታዎ ላይ ያሉ ቋሚ ነገሮችን ማስወገድ ሊያስፈልገው ይችላል። ተቋራጩ የውስጥ የሥራ ቦታዎችን ያጸዳና ጊዜያዊ እና ቋሚ እድሳቶችን ያደርጋል፣ ይህም አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦ የመግቢያ ፓነሎች መትከል፣ የፐላስተር እና የድራይዎል ጥገና፣ ቀዳዳ መሙላት፣ ከዋና ቀለሙ ጋር በማመሳሰል ፕራይም አድርጎ ቀለም መቀባት፣ እና ነባር ንጣፎችን እና ካቢኔቶችን እንደገና ማልበስ እና መተካት። የሥራ ተቋራጩ ውጫዊ የሥራ ቦታዎችን ያጸዳና ጊዜያዊ እና ቋሚ እድሳት ያደርጋል፣ ይህም አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦ የጡብ፣ የሲሚንቶ፣ የግራናይት ወይም የአስፋልት ኩርባዎች፣ የእግረኛ መንገድ፣ አስፋልት፥ የመኪና መግቢያ እና የማቆያ ግድግዳዎች እንዲሁም መሸፈኛ፣ እና ዘር መዝራት፣ የሣር ቦታ እና ተክሎች መተካት። ቋሚ የእድሳት ሥራው በሌላ ጊዜ ይደረጋል። የሥራ ተቋራጩ በተቻለ መጠን ዛፎችን፣ ቁጥቋጦዎችን፣ በሕይወት ያሉ እፅዋትን(ዎች) ላለመንካት ይሞክራል፣ ነገር ግን በመተካት ሥራ ሂደት ላይ በሳር፣ በእጽዋት፣ ወዘተ. ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም። የDC Water እና የሥራ ተቋራጮቹ በቦታዎ ላይ ዕቃዎችን ለማንቀሳቀስ ሊረዱዎት አይችሉም።

3. **በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ DC Water ሥራውን ላይሠራው ይችላል፦** (1) ሠራተኞች የቧንቧውን በታ እንዳይቀይሩ የሚከለክሉ **የተደበቁ አደጋዎች** አሉ፤ (2) የበታው ባለቤትነት የሌላ ሰው ከሆነ እና ባለቤቱ ይህን ፈቃድ ለመፈረም **ካልተስማማ**፤ (3) እርስዎ ወይም ፈቃድ ያለው ሰው የሥራ ተቋራጩ በቀጠሮው ቀን ወደ በታው እንዲገባ ካልፈቀዱ፤ ወይም (4) እርስዎ ወይም ፈቃድ ያለው ሰው በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት **ቤት ከሌላችሁ** እና ሥራውን ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ሳታስይዙ ከቀራችሁ።
4. **ከተተካ በኋላ ለእርስዎ ወይም በታው ላይ ላሉ ነዋሪዎች DC Water ለ6 ወራት የሚቆይ የውሃ ጆግ እና ሁሉንም የሌድ ቅንጣቶችን ለማስወገድ ቧንቧዎችዎን አፍስሶ ለማውጣት የሚከተሏቸው መመሪያዎች ይሰጥዎታል።**

## ትርጓሜዎች፦

1. **ሕንጻ**፦ ውሃው የሚደርሰው ሕንጻ፣ እንደ ቤት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ መዋእለ ሕጻናት፣ ወዘተ.
2. **የኮፐር የውሃ ቱቦ፦** የሚጠጣ ውሃ ለማጓጓዝ የሚያገለግል የብረት ኮፐር ቱቦ።
3. **የሥራ ተቋራጭ**፦ አንድ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት፣ ለምሳሌ የውሃ ቱቦን መተካት የተቀጠረ አንድ ሰው ወይም ኩባንያ።
4. **የዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር**፦ ከሕንጻዎች የሚወጡት የውሃ ቱቦዎች ውሃ ለማግኘት ከመንገድ ሥር የሚገናኙበት ውሃ የሚያጓጉዝ ቱቦ።
5. **የተደበቀ አደጋ**፦ በቀላሉ የማይታይ ነገር ግን ጎጂ ሊሆን ወይም ችግር ሊያመጣ የሚችል ነገር። የተደበቁ አደጋዎች ምሳሌዎች ወደ ጓሮ መብራት የሚወስድ የኤሌትሪክ ወይም የጋዝ መስመርን ወይም ለቤት ማሞቂያ ዘይት የተቀበረ የነዳጅ ታንከርን ሊያካትቱ ይችላሉ።
6. **የሌድ የውሃ ቱቦ፦** ወደ ሕንጻው ውሃ ለማምጣት ከመሬት በታች ከዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር ወደ መጀመሪያው የሕንፃ ግንኙነት የሚዘረጋ ከሌድ የተሠራ ወይም ሌድ የያዘ ቱቦ።
7. **የተረጋገጠ ደብዳቤ**፦ በበታው ባለቤት እና የባለቤቱን ማንነት በሚያረጋግጥ ኖታሪ የተፈረመ ሰነድ።
8. **የግል በታ**፦ ባለቤትነቱ የእርስዎ የሆነ በታ።
9. **የበታ ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው**፦ የበታው ባለቤት የሆነ ሰው ወይም በባለቤቱ ስም እንዲሰራ የተፈቀደለት ሰው።

## የፈቃድ ቅጹን ይሙሉ፣ ይፈርሙ እና ያስረክቡ፦

የቅጹ **ሁለት** ቅጂዎች አሉ። እባክዎን ሁለቱንም የቅጽ ቅጂዎች ይሙሉ (**ፈቃድ** እና **የተደበቁ አደጋዎች**) እና ይፈርሙ (ከታች)። እባክዎን አንድ የተፈረመ ቅጽ ለመዝገቦችዎ ያስቀምጡ እና ሌላውን ለDC Water ያስረክቡ። **ፈቃዱ ከአንድ በላይ በታን የሚመለከት ከሆነ የተያያዘውን ይሙሉ።** የሌድ ውሃ ቱቦውን ለመተካት ዝግጁ ስንሆን፣ የDC Water የሥራ ተቋራጩ የቀጠሮ ጊዜዎቹን ይነግርዎታል። የፈቃድ ቅጹን ለማስረከብ፦

**"Private Lead Service Line Replacement Project/Name and Address" ("የግል የሌድ አገልግሎት መስመር መተኪያ ፕሮጀክት/ስም እና አድራሻ")** በሚል ርእስ አንድ ቅጂ ለled@dcwater.com **ኢሜል** ይላኩ ወይም

አንድ የተፈረመ ቅጽ በሚከተለው አድራሻ **በፖስታ** ይላኩ፦

DC Water - የግል LSL መተኪያ ፕሮጄክት
5000 Overlook Avenue, SW, COF Bldg., 5th Floor
Washington, DC 20032

**ፈቃድ (ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን (1) ብቻ ይምረጡ እና እባክዎ ሁሉንም ክፍሎች ይሙሉ)፡-**

_________የመግቢያ ፈቃዱን አንብቤያለሁ እና DC Water እና የሥራ ተቋራጩ በቦታዬ ላይ ያለውን የሌድ የውሃ ቱቦ እንዲተኩ ፈቃድ ለመስጠት **እስማማለሁ**። ሥራው በሚከናወንበት ጊዜ እኔ ወይም የተፈቀደለት ሰው እንገኛለን።

_________የመግቢያ ፈቃዱን አንብቤያለሁ እና DC Water እና የሥራ ተቋራጩ በቦታዬ ላይ እንዲገቡ **አልፈቅድም**። ለሌድ መጋለጥ በተለይ በነፍሰ ጡር ሴቶች እና በትናንሽ ሕጻናት ላይ ከባድ የጤና ችግር እንደሚያስከትል ተረድቻለሁ። ሌድ ኩላሊቶችን እና አንጎልን ሊጎዳ ይችላል እናም ከነርቭ እድገት ጉድለቶች ጋር ተቆራኝቷል። የኩላሊት ችግርና ከፍተኛ የደም ግፊት ያለባቸው አዋቂዎች ከጤናማ ሰዎች በበለጠ በትንሽ የሌድ መጠን ሊጎዱ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በአገልግሎት መስመር ስራ ወቅት የሌድ ቧንቧ መቁረጥ ወይም ሌላ አካላዊ መስተጓጎል በውሃ ውስጥ የሚለቀቀው ሌድ እንዲጨምር እንደሚያደርግ ተረድቻለሁ። ስለዚህ፣ ምንም እንኳን በብርቱ ቢበረታታም፣ ከሕዝቡ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ የሌድ ውሃ ቱቦ መተካትን **አልስማማም**። በመጨረሻ፣ በD.C. ሕግ ቁጥር 22-0241 መሠረት ቤቴ ሲሸጥ ወይም ሲከራይ የሌድ ውሃ ቱቦ እንዳለ ይፋ መደረግ እንዳለበት አውቃለሁ።

የንብረት ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው ስም፡-______________________________ ኢሜል፡- ______________________________

ፈቃድ ያለው ሰው (ነዋሪ ወይም ሌላ አካል) ከባለቤቱ ባለ ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም ባለቤቱን እንዲወክሉ የሚፈቅድ ሌላ ሕጋዊ ሰነድ ማቅረብ **ይኖርበታል**። ጥያቄ ካልዎት LFDCን ያነጋግሩ።

ፊርማ፡- ______________________________ ቀን፡- ________________ ስልክ ቁጥር፡- ________________________

የንብረት አድራሻ፡- ____________________________________ ፖስታ የመላኪያ አድራሻ፡- ______________________________

**የባለብዙ ንብረት አድራሻ ዝርዝር ተያይዟል** (የሚመለከት ከሆነ)

____________________________________ ____________________________________

**የተደበቁ አደጋዎች፡-**

ስለ ማንኛውችም የሚታወቁ **የተደበቁ አደጋዎች** ወይም በቅርብ ጊዜ በግል ቦታዎ ላይ ሥራን የሚከለክሉ ወይም ሠራተኞችን ሊጎዱ ስለሚችሉ የቧንቧ ሥራዎችን በተመለከተ ለDC Water እና/ወይም ለሥራ ተቋራጩ ማሳወቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው። እባክዎን እዚህ የዘርዝሯቸው እና ምንም ከሌለ፣ "ምንም" ብለው ይጻፉ፡-

______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________

ለጥያቄዎች ወይም ለእርዳታ፣ እባክዎን Lead Free DCን በሚከተለው ያነጋግሩ፡-

(202) 787 - 4044 ወይም lead@dcwater.com

**አባሪ - ለባለ ብዙ ንብረቶች የአድራሻ ዝርዝር**

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የበርካታ ንብረቶች ባለቤት ከሆኑ እና በነጻ፣ ምንም ወጪ የሌለበት የሌድ አገልግሎት መስመር መተካት ለሁሉም ንብረቶችዎ በአንድ የመግቢያ ፈቃድ ቅጽ መፍቀድ ከፈለጉ፣ እባክዎ ይህን ቅጽ ይሙሉ እና ከመግቢያ ፈቃድዎ ጋር ያስገቡት።

በቦታው ላይ ያለው ወይም ዋና እውቂያው የመግቢያ ፈቃድ ቅጹ ገጽ ሁለት ላይ ከተጠቀሰው ሰው የተለየ ከሆነ እባክዎ ለእያንዳንዱ ቦታ መገናኛ መረጃ ያቅርቡ።

| የንብረቱ አድራሻ | በቦታው ላይ የሚገኘው ሰው | | | | በቦታው ላይ ያሉ ማናቸውንም የተደበቁ አደጋዎች ይግለጹ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ስም** | **ስልክ ቁጥር** | **አማራጭ ስልክ** | **ኢሜል** | |
| *ምሳሌ*<br>*123 F Street NW* | *Parker Taylor* | *202-111-1111* | *202-222-2222* | *ptaylor@aol.com* | *ከባድ ዝናብ ሲዘንብ ምድር ቤቱ ይጥለቀለቃል* |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

_________የመግቢያ ፈቃዱን አንብቤያለሁ እና DC Water እና የሥራ ተቋራጩ በቦታዬ ላይ ያለውን የሌድ የውሃ ቱቦ እንዲተኩ ፈቃድ ለመስጠት **እስማማለሁ**። ሥራው በሚከናወንበት ጊዜ እኔ ወይም የተፈቀደለት ሰው እንገኛለን።

የንብረት ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው ስም፡-________________________________ ኢሜል፡- __________________________________
ፈቃድ ያለው ሰው (ነዋሪ ወይም ሌላ አካል) ከባለቤቱ ባለ ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም ባለቤቱን እንዲወክሉ የሚፈቅድ ሌላ ሕጋዊ ሰነድ **የግድ** ማቅረብ ይኖርበታል። ጥያቄ ካልዎት LFDCን ያነጋግሩ።
ፊርማ፡- ___________________________________ ቀን፡- ___________________ ስልክ ቁጥር፡- __________________________